# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 3 ልዩ ጥናታዊ ዕትም ግንቦት 4 ቀን 2011 ዓ.ም.

## ኢትዮጵያዊነትን ያማከለ አስተዳደራዊ አከላለል

ይህ በ"አንድ ሀገር አንድ ሕዝብ ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" ታህሳስ 11 ቀን 2011 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው። ይድረሳቸው አይድረሳቸው የተሰጠን ምላሽ ባይኖርም በወቅቱ ለጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በፖስታ ተልኳል።

በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገ አከላለል ያብቃ ስንል ያለው አማራጭ ይህ ብቻ ነው ለማለት ሳይሆን በኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንናቄ በኩል ያቀረብናቸው ሦስት አማራጮችን አዎንታዊና አሉታዊ ጎኖቹን በመጥቀስ ለውይይት ያቀረብነውን ሠነድ ለሕዝብ በመልቀቅ ውይይት ይደረግበት ዘንድ እንጋብዛለን።

መልካም ንባብ

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ!

አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ።

ኢትዮጵያችን

# አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ

ኢትዮጵያዊነትን ያማከለ አስተዳደራዊ አከላለል ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ግንባታ

ለውይይት የቀረበ ሠነድ

## ሀ. የቀድሞው ክፍለ ሀገራዊ አስተዳደር

## ለ. አውራጃን ያማከለ አስተዳደር

## ሐ. መልክዓ ምድር ተፋሰስ ወንዞች አከላለል

መጀመሪያ ዕትም፦ ሐምሌ 16 ቀን 2010 ዓ.ም.

ሁለተኛ፦ በኢትዮጵያችን ቅጽ 3 ቁጥር 2 ዕትም የወጣ ህዳር 7 ቀን 2011 ዓ.ም.

ሦስተኛ ዕትም፦ ታህሳስ 1 ቀን 2011 ዓ.ም.

አራተኛ ዕትም ፦ ግንቦት 4 ቀን 2011 ዓ.ም.

(703) 300 4302 USA

Ethiopiachen2009@gmail.com

www.ethiopiachen.org

ግንቦት 4 ቀን 2011 ዓ.ም. (May 12, 2019)

የዚህ ሠነድ የባለቤትነት መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

ኢትዮጵያችን

## የፅሁፉ ፍሬ ሀሳቦች

በኢትዮጵያችን ያለውን በዘርና በቋንቋ ላይ የተመሠረተው የክልል አስተዳደር በዜግነትና አብሮነት ያደረሰውን ጉዳት ሊያክሙ የሚችሉ አማራጭ ሃሳቦችን ያቀርባል። የቀረቡት ሦስቱም አማራጮች በዘርና በቋንቋ ሳይሆን ለመንግሥት አስተዳደር፣ ለልማትና ዕድገት አመቺነት ላይ ብቻ ያተኮሩ ናቸው። የመጀመሪያው ሃሳብ ከሃያ ስምንት ዓመታት በፊት የነበረው ኢትዮጵያን በክፍለ ሀገራት አዋቅሮ ማስተዳደር ሲሆን ጎጂ ጎኑንም ይጠቁማል። ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ አገሪቱን በጠቅላላ በቀድሞው ክፍለ ሀገራት ውስጥ በነበሩት ወደ ዘጠና የሚሆኑ አውራጃዎችን ከፍሎ ማስተዳደር ሃሳብ ነው። የመጨረሻው አማራጭ ከሁለቱ ለየት ያለ ሆኖ ኢትዮጵያን በአሥር መልክዓ ምድር የወንዝ ተፋሰስ ቀጠናዎች ከፍሎ የማስተዳደር ስልት ነው። ***"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** በወንዝ ተፋሰስ ቀጥናዎች የማስተዳደር ስልቱ የተሻለ ነው ብሎ ያምናል ለዚህም ለንፅፅር የሚረዱ ምክንያቶችን ያቀርባል።

## መነሻ ምክንያቶች

ኢትዮጵያ እንደሌሎች የዓለማችን ሀገራት ሁሉ በቀጠናዎች የምትከፈለው በቅድሚያ በመሠረታዊነት ለመንግሥት አስተዳደር፣ በጀትና የልማት ዕቅድና ተያያዥ ጉዳዮችን ለማከናወን እንዲያመችና ለማቀላጠፍ እንዲቻል ነው። ለነዚህ አስተዳደር ቀጠናዎች የሚዋቀሩበት ዋናው መስፈርት ወይም መለኪያ የመንግሥትን አሠራር እንዲያግዝ ሲሆን የሕዝብ አሰፋፈርና ብዛት፣ እንዲሁም ባህልና ሌሎችም ተጨባጭ ሁኔታዎችንም ከግምት ውስጥ ያስገባል። በሀገር አቀፍ ደረጃና በየአስተዳደር ቀጠናዎች የሚከናወኑት የመንግሥት ተግባርና ሀላፊነቶች ጠቅለል ባለ መልኩ እነዚህ ይሆናሉ፡-

- የግለሰብ ዜጎችን፣ የሕብረተሰብና በአጠቃላይ የሕዝብን መብት፣ ሰላምና ደህንነት ማረጋገጥ
- የልማትና ዕድገት ዕቅዶችን (ማለትም የመገናኛ፣ የጤና፣ የትምህርት፣ የኃይል አቅርቦት ወዘተ) ማውጣትና ተከታትሎ የማስፈፀም ተግባር፣ ሃላፊነትና ተጠያቂነት
- የሀገሪቱን ድንበርና ሉዓላዊነት ማስጠበቅና ከአጎራባች አገሮችና በዓለም የፖለቲካ፣ ዲፕሎማሲ፣ የገንዘብና የተለያዩ ተቋማት ጋር ያላትን ግንኙነት በብሔራዊ ጥቅሟና ፍላጎቷ መሠረት መከታተልና ማስፈፀም ይሆናሉ።

የሀገር በአስተዳደራዊ ቀጠናዋች መከፈል እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን የመንግሥትን ሃላፊነትና ተግባርን፡ ግልፅነትና ተጠያቂነትን በሚያግዝ መልኩ ለማዋቀር ነው።

የሀገራችን የየቀጠናው የአስተዳደር መዋቅሮች ሃላፊነትና ተግባር ከበሔራዊ/ማዕከላዊ/ፌዴራላዊ መንግሥት ጋር በሕግና ደንብ የተመሠረቱ የሥራ ግንኙነቶችና የተግባርና ሃላፊነት ወሰንና ድንበር እንዲሁም የዕዝ ተዋረድ ያስፈልጋቸዋል። የብሔራዊው መንግሥትም ሆነ የአስተዳደር ቀጠናዎች የጋራ ዓላማ ከላይ ጠቅለል ብለው የተጠቀሱትን ተግባራትና ሃላፊነቶች በመተጋገዝ ማስፈፀም ለመላው ሕዝብ የተሰጠ የአደራ ግዴታ ነው።

## የተከሰቱ ችግሮች

ከነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት ዓላማዎች፡ ተግባርና ሃላፊነቶች በማንኛውም መልክና ደረጃ የማይጣጣም ወይም ቅራኔ የሚፈጥር የሀገር አስተዳደራዊ አወቃቀር እንደ አስፈላጊነቱና አግባብ ባለው ክፍል እየታረመና እየተስተካከለ ካልሄደ የሚፈጠረው ችግር አሁን በኢትዮጵያ እየታየ ካለው አካባቢያዊ የማንነት ግጭት የባሰም ሊሆን ይችላል።

ጥቂቶቹን በአስተዳድር ክልሎችና በፌዴራል መንግሥቱ ግንኙነትና የሃላፊነት ክፍተቶች የተፈጠሩ ችግሮች

- ክልሎች የራሳቸው የሆነ "ልዩ ፖሊስ" ፦ የዚህ ሥርዓት አልባ ልዩ ኃይልና (Paramilitary) መሪው ተቋም ያለው የሰው ብዛት፣ በጀትና ሥልጠና፣ ሥምሪትና ዕዝ ሌሎችም ጉዳዮች ከፌዴራል መንግሥት ቁጥጥር የወጣ መሆኑ በሶማሊያ፣ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በትግራይና በሌሎች ክልሎችም ይህ "ልዩ ፖሊስ" ያደረሰው ጉዳት ግልፅ ነው።
- በየክልሉ ያሉ ንዑስ ነገዶች/ጎሳዎች/ብሔረሰቦች የክልሉ አስተዳደርም ሆነ በእርሱ የሚታዘዘው "ልዩ ፖሊስ" ለዜግነት መብታቸው በመቆምና መከላከል ፋንታ ወይ ሲያፈናቅል አልያም መብታቸው ሲጣስ አይቶ እንዳላየ ይሆናል
- በየክልሉ የተፎካካሪ ፓርቲዎችን እንቅስቃሴ የመገደብና የማፈን ባሕል እየተስፋፋ ነው

እነዚህ ለናሙና የተጠቀሱት ችግሮች መንግሥት የራሱና የየቀጠና አስተዳደር ግንኙነቶች በሕግ ገደብ ካልተያዙ፣ የተጠያቂነት ክፍተቶች ካሉና በየጊዜው እየታረሙ፡ እየተስተካከሉና መፍትሔ እየተበጀላቸው ከልሄደ ችግሩ እየተባባሰ ሄዶ የሕዝብ ሰላምና ደህንነት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ህልውና ራሱ ይፈታተናል።

## ማሳሰቢያ

ከላይ ለማሳያ ያህል የተጠቀሱትና ሌሎችም በርካታ ችግሮች እንዲሁ ከዚህ በታች በ "*አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ*" ለውይይት ከቀረቡት የሀገር አስተዳደር አማራጭ ሀሳቦች በቀጥታም በተዘዋዋሪም አሁን ያለውን ሕገ መንግሥት መሻሻል ወይም ሙሉ ለሙሉ መለወጥ ያስፈልጋቸዋል።

# መግቢያ

በ "*አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ*" አመለካከት ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜትን አጉልቶ ለማውጣት ቀጣዩ የሀገራችን የግዛት አከላለል አስመልክቶ ሦስት አማራጮች እናቀርባለን። የአቀረብናቸው አማራጭ አከላለሎችን በሥዕላዊ መግለጫ ጭምር ለማስቀመጥ ሞክረናል። ወደፊት አሁን ከአለው በተከበሩ ጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከሚመራው አስተዳደርና ከሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችና ታዋቂ ግለሰቦች ጋር በሚደረግ የጋራ ጥናትና ውይይት ዳብሮ ለሕዝብ ይቀርብ ዘንድ የራሳችንን አማራጮች ለውይይት አቅርበናል።

በዚሁ መሠረት ዘርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገ የግዛት አከላለል ያበቃ ዘንድ ድምጻችንን እናሰማለን፣ እንታገላለንም። ደጋግመን እንዳስቀመጥነው ዘርንና ቋንቋን መሰረት ያደረገ አከላለል ለሀገር እድገትም ሆነ ልማት ጠቀሜታ የለውም፣ ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜትን ሸርሻሪ በመሆኑ በአዲስ መልክ ይካለል ዘንድ ሀሳባችንን እነሆ!

በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና አካላት ሊቀርቡ የሚችሉ የወደፊቷን ኢትዮጵያ አከላለል ሀሳቦች ሳናናንቅ የኛን ምልከታ እናቀርባለን።

ያቀረብናቸው ዘርና/ቋንቋን መሠረት ያላደረጉ አከላለሎች እንደ አካባቢያቸው ስፋትና ሕዝብ ብዛት ማዕከላዊ መንግስት በሚመድበው ዓመታዊ በጀት ሙሉ በሙሉ ክፍለ ሀገራቸውን/አውራጃቸውን/ተፋሰሳቸውን የማስተዳደር ኃላፊነት ይወስዳሉ።

የሁሉም የሀገሪቷ ብሔራዊ ቋንቋ አማርኛ ሲሆን በየክፍለ ሀገራቱ/አውራጃዎቹ/ተፋሰሶቹ የሚነገሩ ቋንቋዎች፣ እምነቶችና ባህሎች ይዳብሩ ዘንድ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል።

የሀገሪቷ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ በአግድሞሽና በላዩ ላይ ምንም ምልክት የሌለው አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ሲሆን እያንዳንዱ ክፍለ ሀገር/አውራጃ/ተፋሰስ የራሱ መለያ ዓርማ ሊኖረው ይችላል።

ወደፊት በሚኖረው የሀገሪቷ ምክር ቤት እያንዳንዱ ክፍለ ሀገር/አውራጃ/ተፋሰስ በእኩል ድምጽ ወይም እንደ ክፍለ ሀገር/አውራጃ/ተፋሰስ ሕዝብ ብዛት የፓርላማ ውክልና ይኖረዋል።

ይህ አወቃቀር በተለምዶ በየአንዳንዱ ክፍለ ሀገር/አውራጃ/ተፋሰስ አስተዳደራዊ ክልል የኅብረተሰቡ ጥረት ክልሉን እንዲያለማና ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አስተዳደር ለማዋቀር ምቹና ቀላል ያደርገዋል። በሌላም በኩል ለ28 ዓመት የተሰነቀረብንን ዘረኝነትና የዘር አከላለል "ይህ የኔ ብቻ ነው" አስተሳሰብ ወደ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜት እንዲያድግ ይረዳል።

አዲስ አበባ አዲስ የተመሠረቱ መንደሮችን አካቶ በደርግ ጊዜ በነበረው ከፍተኛና ወይም በወረዳና አውራጃ መልክ ማዋቀሩ ለአሠራር ቀለል ያለ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

<u>**ማስታወሻ**</u>

**በሠነዱ ላይ የተካተቱት ሥዕሎች ከተለያዩ ምንጮች በጎልጉል** (Googul) **የተገኙትን በማዳበር ነው።**

**በዲጂታል** (Digital) **መልክ የተሠሩት የሀገራችን ኢትዮጵያ መልክዓ ምድርና ተፋሰስ ካርታዎች** (Maps) **በጎልጉል መልክዓ ምድር** (Googul Earth), Map Info, Adobe Photo Shop **ጣምራ መልክዓ ምድር የመረጃ ምንጮች** (Geographics Information Systems) Software's **ያጠናከርናቸው ናቸው።**

**ለማንኛውም አስተያየትና ውይይት ቀጥሎ ባለው ኢሜል ይላኩልን፣ ስልክ ይደውሉልን። ድረ ገፃችንንም ይጎብኙ።**

(703) 300 4302 USA **ነሲቡ ስብሐት፤ ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ ሊቀ መንበር**

Ethiopiachen2009@gmail.com


www.ethiopiachen.org

**ግንቦት** 4 **ቀን** 2011 **ዓ.ም.** (May 12, 2019)

**የዚህ ሠነድ የባለቤትነት መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።**


ኢትዮጵያችን

# ሀ. የቀድሞው ክፍለ ሀገራዊ አስተዳደር





*ምሥል 1.0. የቀድሞው 14ቱ ኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት አከላለል በውስጡ ከያዟቸው አውራጃዎች ጋር*

*ምሥል 1.1. የቀድሞው 13ቱ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት*




ይህ አከላለል ኢትዮጵያን ከኤርትራ በቀር በ13 ክፍለ ሀገራት አስተዳደሮች ያካልላታል። በዚህ አከላለል አሁን ከአለው ዘርንና ቋንቋን መሠረት ከአደረገው አከላለል ቢሻልም የተወሰኑ ብሔረሰቦችን በአንድ የዘር ክልል ወይም የማንነት ዝንባሌ ውስጥ ያስቀምጣል። ለምሳሌ ትግራይ ክፍለ ሀገር አሁንም የዘርና የቋንቋ አከላለልን መያዙን ያመለክታል። ጎንደር፣ ጎጃም ወሎ የመሳሰሉትም በአማራ ብሔረሰብ ውስጥ የእኔነት ስሜትን መፍጠራቸው አይቀሬ ነው። እንዲሁም ወለጋ፣ አሩሲ መሰል ክፍለ ሀገራትም እኛነን ኦሮሞ የሚል የማንነት ስሜትን እንደሚያጎላ ይገመታል። በሌላም በኩል እንደ አፋር የመሳሰሉ ራስ ገዝ አስተዳደሮች እንዲዋጡ ያደርጋል። በተለይ የኢሕአዴግ የዘርና ቋንቋ አከላለል የጣለውን የዘረኝነት ስነልቦናዊ ጥቃት እንደያዙ ወደዚህ ክፍለ ሀገራዊ አስተዳደር መሸጋገሩ ችግሩን በመጠኑ ከማቃለል ሌላ ሙሉ በሙሉ መፍትሄ ያስገኛል ወይ? የሚለውን በጥያቄ ያስቀምጠዋል።

# ለ. አውራጃዎችን ያማከለ አስተዳደር




*ምሥል 2.0. የቀድሞው 94ቱ ኢትዮጵያ አውራጃዎች*

`


***"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** የወደፊቷን ኢትዮጵያ የግዛት አከላለል በሁለተኛ ደረጃ እንደ አማራጭ ያቀረብነው ሠነድ ነው። በዚሁ መሠረት በየክፍላተ ሀገሩ ያሉትን አውራጃዎች በዝርዝር አስቀምጠናል። ሠነዱ ወደፊት በተጠናከረ መልኩ ሰፊ ትንተናን ይዞ ይዘጋጃል። ይህ የግዛት አከላለል በአውራጃ ደረጃ ነዋሪው ኅብረተሰብ ዘርና ቋንቋን ሳይመለከት አካባቢውን በማልማትና በማሳደግ ሂደት ላይ ትኩረት እንዲሰጥ ይረዳል የሚል ግንዛቤ አለን።

አስተዳደርና ኢኮኖሚን በሚመለከት ኢትዮጵያ ቀድሞ በአሏት አውራጃዎች መሠረት የወደፊት አከላለሏ ይሆን ዘንድ በምሥል (2.1) እና (2.2) እንደተቀመጠው እናቀርባለን። በዚህም መሠረት በሀገሪቷ በአጠቃላይ 94 አውራጃዎች (አዲስ አበባን ሳይጨምር) የራሳቸው ራስ ገዝ አስተዳደር ኖሯቸው እንዲዋቀር አቅርበናል።

በ "***አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" መሠረት ጥንት በዓፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ የነበረው ጠቅላይ ግዛት አጠራር እና በደርግ ጊዜ የነበረው ክፍለ ሀገር አጠራር ተቀይሮ የእያንዳንዱ አውራጃዎች አጠራር ስማቸውን ይዞ ***"ክፍለ ኢትዮጵያ"*** ይባል ዘንድ ሀሳብ እናቀርባለን (ለምሳሌ ከጎሙጎፋ አውራጃዎች ብንወስድ ጋሞ ክፍለ ኢትዮጵያ፣ ገዶሌ ክፍለ ኢትዮጵያ ወዘተ እየተባሉ ይጠራሉ)።


ይህ አጠራር ሁሉም አውራጃዎች የኢትዮጵያ አካልነታቸውን ይበልጥ ትኩረት ከመስጠት አኳያ ጠቀሜታው የጎላ ነው።

የእያንዳንዱ አውራጃ ክፍለ ኢትዮጵያ ግዛቶች ምሥል (2.2 እና 2.3) ካርታና የአውራጃዎቹ ሠንጠረዥ በአባሪነት በተያዘው ገጽ ይመልከቱ።





*ምሥል 2.1. የቀድሞው ኢትዮጵያ አውራጃዎች*

*ምሥል 2.2. የቀድሞው 94ቱ የኢትዮጵያ አውራጃዎች*






*ምሥል 2.3 የኢትዮጵያ አውራጃዎችን በየክፍለ ሀገሩ የሚያሳይ*





WELEGA
DISTRICT MAP
የወለጋ አውራጃዎች
ASOSA
WELEGA
GIMBI
HORO GUDRU
Shambu
NEKEMT
KELEM
ARJO
Dembidolo



Mehal Meda
EFESON
MERHABETE
Alem Ketema
MENZ & GISHE
YFAT & TIMUGA
Fiche
SELALE
Debre Birhan
SHEWA
TEGULET & BULGA
JIBAT & MECHA
MENAGESHA
Ambo
ADDIS ABABA
YERER & KEREYU
Nazret
Weliso
CHEBO & GURAGE
Ziway
SHEWA
DISTRICT MAP
የሸዋ አውራጃዎች
HAYKOCH & BUTAJIRA
Hosaina
KEMBATA & HADIA



KEFA
DISTRICT MAP
የከፋ አውራጃዎች
LIMU
Agaro
JIMA
KEFA
Bonga
Waka
Mizan Teferi
KEFA
KULO KONTA
GIMIRA
Maji
MAJI & GOLDIYA



SOR & GEBA
Bedele
METU
GAMBELA
BUNO BEDELE
GORE
ILUBABOUR
MOCHA
Masha
ILUBABOUR
DISTRICT MAP
ኢሉባቦር አውራጃዎች


GAMO
GOFA
Felege Neway
ARBA MINCH
GAMO GOFA
Jinka
Gidole
GARDULA
GELEB & HAMER BAKO
GAMO GOFA
DISTRICT MAP
የጋሞ ጎፋ አውራጃዎች


WELAYITA
Sodo
AWASA
SIDAMA
SIDAMO
DISTRICT MAP
የሲዳሞ አውራጃዎች
Dila
GODE
Kibre Mengist
JEMJEM
ARERO
Negele
Yabelo
SIDAMO
BORENA


Tinsaye
Birhan
ARBA GUGU
ASELA
Robi
TICHO
CHILALO
ARUSI
DISTRICT MAP
የአሩሲ አውራጃዎች



BALE GOBA
DISTRICT MAP
የባሌ ጎባ አውራጃዎች
Dodola
GENALE
GOBA
Ginir
WABE
BALE
MENDEYO
Mena
DELO
EL KERE


HARERGE
DISTRICT MAP
የሐረርጌ አውራጃዎች
CHERCER ADAL &
GARA GURACHA
ISA & GURGURA
Dire Dawa
JIJIGA
Jijiga
HARER
Harer
Zuriya
Funyan
Bira
Deder
WEBERA
Girawa
Asbe Teferi
Gelemso
HABRO
GARA
MULETA
GURSUM
Degeh Bur
DEGEH BUR
HARERGE
WELWEL & WARDER
Warder
Kebri Dehar
KEBRI DEHAR
GODE
Gode
Kelafo
KELAFO

*ሠንጠረዥ ሀ. የቀድሞ ኢትዮጵያ አውራጃዎች ስም በየክፍለ ሀገራቱ አኳያ*


| | | | |
|---|---|---|---|
| **ትግራይ** | **ጎንደር** | **ጎጃም** | **ወለጋ** |
| **አውራጃ** | **አውራጃ** | **አውራጃ** | **አወራጃ** |
| እንደርታ | ጎንደር | ደብረ ማርቆስ | አሶሳ |
| ተምቤን | ጭልጋ | ባህር ዳር | ቄለም |
| አጋሜ | ሰሜን | አገው ምድር | ጊምቢ |
| አድዋ | ደብረታቦር | ቆላ ደጋ ዳሞት | ሆሮ ጉድረ |
| አክሱም | ጋይንት | መተከል | ነቀምቴ |
| ራያና አዘቦ | ሊቦ | ሞጣ | ኢርጀ |
| ሽሬ | ወገራ | ብቸና | |
| ሁለት አውላሎ | | | |
| | | | |
| **ሸዋ** | **ወሎ** | **ሐረርጌ** | **ከፋ** |
| **አውራጃ** | **አውራጃ** | **አውራጃ** | **አውራጃ** |
| መራሕቤቴ | ደሴ ዙሪያ | ሐረር ዙሪያ | ጊሚራ |
| ሰላሌ | ዋግ | ጨርጨር አዳልና ጋራ ጉራቻ | ማጂ |
| መንናገሻ | ላስታ | ጅጅጋ | ጐልደሃ |
| መንዝና ጊሼ | ራያና ቆቦ | ሐብሮ | ሊሙ |
| የረርና ከረዩ | ዋድላ ደላንታ | ሂሳና ጉርጉራ | ጅማ |
| ጅባትና ሜጫ | የጁ | ወበራ | ከፋ |
| ይፋትና ጥሙጋ | አምባሰል | ጋራ ሙለታ | ኰሎ ኮንታ |
| ተጉለትና ቡልጋ | ወረሂመኑ | ግርሱም | |
| ጨቦና ጉራጌ | ቦረና | ደግሃ ቡር | **አርሲ** |
| ሐይቆችና ቡታጅራ | ወረሂሉ | ጎዴ | **አውራጃ** |
| ከምባታና ሃዲያ | ቃሉ | ቀላፎ | ጭላሎ |
| | አውሳ | ቀብሪ ደሃር | ጢቾ |
| | | ወልወልና ዋርዴር | አርባጉጉ |
| | | | |
| **ገሙ ጎፋ** | **ኢሉባቦር** | **ሲዳሞ** | **ባሌ** |
| **አውራጃ** | **አውራጃ** | **አውራጃ** | **አውራጃ** |
| ጐፋ | ጋርዱላ | ሲዳሞ | ገናሌ |
| ጋሞ | ሞቻ | ጌድዮ | ዶሎ |
| ገለብና ሐመር ባኮ | ጐሬ | ቦረና | ምንድዮ |
| ጋሪዱላ | ቡኖ | ወላይታ | ዋቢ |
| | ሶርና | ጀምጀም | አልከሬ |
| | | አሬሮ | |
| | | | |

# ሐ. መልክዓ ምድራዊ ተፋሰስ ወንዞች አስተዳደር




*ምሥል 3.0. 10ሩ የኢትዮጵያ ተፋሰስ ውንዞች ከሚያካትቷቸው ክፍለ ሀገራትና አውራጃዎች ጋር*

*ምሥል 3.1. 10ሩ የኢትዮጵያ ተፋሰስ ወንዞች አስተዳደራዊ አከላለል*






መልክዓ ምድር (ጂኦግራፊያዊ) የኢትዮጵያ ወንዞችንና ተፋሰሶችን አከላለል አማክሎ ሲካለል የየክልሉም አጠራር በተፋሰሱ ወንዞች ይሆናል። ይህ ያለውን የሀገሪቷን አከላለል ብዛት ሲያሳንሰው በሌላ በኩል ደግሞ የተለያዩ ጎሳዎች/ነገዶችን/ብሔረሰቦችን አብሮ የመኖር ትስስርን ይበልጥ ያጠነክረዋል። ይህ አከላለል በግለሰብ ደረጃ እንኳ ጎሳዬ/ነገዴ/ብሔሬ ከዚህ ነው ያስብላል እንጂ ክልሌ ይህ ነው የሚለውን በማስወገድ ጥሩ ጠቀሜታ ይኖረዋል። የተፋሰሶች አከላለልና ስያሜ በምሥል 3.1 እንደተመለከተው አዲስ አበባን ሳያካትት ብዛታቸው 10 ሲሆን ስያሜአቸውም ተከዜ ክፍለ ኢትዮጵያ፣ አፋር ክፍለ ኢትዮጵያ፣ ዐባይ ክፍለ


ኢትዮጵያ፣ አዋሽ ክፍለ ኢትዮጵያ፣ ባሮ አኮቦ ክፍለ ኢትዮጵያ፣ ኦሞ ክፍለ ኢትዮጵያ፣ ስምጥ ሸለቆ ክፍለ ኢትዮጵያ፣ ገናሌ ዳዋ ክፍለ ኢትዮጵያ፣ ዋቢ ሸበሌ ክፍለ ኢትዮጵያ እና ኦጋዴን ክፍለ ኢትዮጵያ ይሆናል። ተፋሰስ የሚለውን ሁሉም የኢትዮጵያ አካል ስለሆኑና ይህን ይበልጥ ለማጠናከር ክፍለ ኢትዮጵያ በሚለው መተካቱ ኢትዮጵያችንን ይበልጥ ያጎላታል። ይህ አከላለል ሌላው ጠቀሜታው ሁሉንም ዘር ትግሬውን ከሌላው፣ አማራውን ከሌላው፣ ኦሮሞውን ከሌላው፣ ሌላውንም ከሌላው ቀይጦ ስለሚያካልል በሂደት ለሀገራችን ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜትን ይበልጥ እንድናዳብር ይጠቅማል። ይህ ሲሆን ባህላችንን፣ ቋንቋችንን፣ ሃይማኖታችንንና በሂደትም ዘራችንንም አብሮ በመኖር፣ በመጋባት እየተጋራን ያሉንን ቋንቋዎችና የተለያዩ ባህላዊ እሴቶች እንዳይረሱ ደግሞ ሁሉም ኃላፊነት ወስዶ እንዲያዳብረው፣ እንዲንከባከበው ይረዳል።


የኢትዮጵያ ተፋሰስ ወንዞችን አስታኮ የቀረበው አስተዳደራዊ ክልል ውስጥ እያንዳንዱ ተፋሰስ የሚያካትታቸው የድሮ አውራጃዎችና ክፍለ ሀገራት ከታች በቀረቡት ምሥል 3.2 መግለጫዎችና ሠንጠረዦች ተቀምጠዋል።


*ምሥል 3.2. የኢትዮጵያ ተፋሰስ ወንዞች አከላለል ከሚያካልሏቸው አውራጃዎች ጋር በተናጥል*






ABAY RIVER BASIN
GOJAM
ABBAY BASIN
WELEGA
SHEWA
WELLO



AWASH RIVER BASIN
WELLO
AWASH BASIN
SHEWA
HARER



BARO AKOBO RIVER BASIN
WELEGA
BARO AKOBO BASIN
ILLUBABOUR
OMO GIBE BASIN
GAMO GOFA


OMO GIBE
RIVER BASIN
JIMA KEFA
OMO GIBE BASIN
RIFT VALLEY BASIN
GAMO GOFA
ARBA MINCH
Image Landsat / Copernicus


RIFT VALLEY
RIVER BASIN
ARUSI
ASELA
AWASA
RIFT VALLEY BASIN
ARBA MINCH
GENALE DAWA BASIN
GORDULA
Image Landsat / Copernicus


GENALE DAWA RIVER BASIN
BALE
HARERGE
GENALE DAWA BASIN
SIDAMO
BORENA
EL KERE


WABI SHEBELE
RIVER BASIN
WABI SHEBELE BASIN
HARERGE
OGADEN BASIN
BALE


OGADEN
RIVER BASIN
JIJIGA
DEGEHA BUR
OGADEN BASIN
HARERGE

## 1. የሚያካትቷቸው ክፍለ ሀገራት

| የተፋሰስ ስም | የሚያካትቷቸው ክፍለ ሀገራት |
|---|---|
| ተከዜ | ምዕራብ ትግራይ፣ሰሜን ጎንደር፣ሰሜን ምዕራብ ወሎ |
| አባይ | ደቡብ ጎንደር፣ ሙሉ ጎጃም፣ ደቡብ ምዕራብ ወሎ፣ ሰሜን ምዕራብ ሸዋ፣ ሰሜን ምሥራቅ ወለጋ፣ ምሥራቅ ኢሉባቡር፣ ሰሜን ምዕራብ ከፋ |
| ባሮ አኮቦ | መካከለኛውና ምዕራብ ኢሉባቡር፣ ምዕራብ ከፋ፣ ደቡብ ምዕራብ ወለጋ |
| አፋር | ምሥራቅ ትግራይ፣ ሰሜን ምሥራቅ ወሎ |
| አዋሽ | ደቡብ ምሥራቅ ወሎ፣ ሰሜን ምሥራቅ ሸዋ፣ ሰሜን ሐረርጌ፣ ሰሜን አሩሲ |
| ኦሞ ጊቤ | መካከለኛው ሰሜን ምሥራቅ ከፋ፣ ደቡብ ምሥራቅ ሸዋ፣ ሰሜን ምዕራብ ጎሙጎፋ፣ በከፊል ሰሜን ምዕራብ ሲዳሞ |
| ስምጥ ሸለቆ | ደቡብ ምሥራቅ ሸዋ፣ ምዕራብ ሲዳሞ፣ ምሥራቅ ጎሙ ጎፋ፣ ደቡብ ምዕራብ አሩሲ |
| ዋቢ ሸበሌ | ምሥራቅ አሩሲ፣ ምሥራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ሐረርጌ |
| ገናሌ ዳዋ | ደቡብ ሲዳሞ አብዛኛውን፣ ምዕራብ ባሌ |
| ኦጋዴን | ምሥራቅ ሐረርጌ |
| | |

ኢትዮጵያ


ምዕ = ም ዕራብ ምሥ = ምሥራቅ ሰ = ሰሜን ደ = ደቡብ መ = መካከለኛው

## 2. የሚያካትቷቸው አውራጃዎች

| የተፋሰስ ስም | የሚያካትቷቸው አውራጃዎች |
| --- | --- |
| ተከዜ | **ከትግራይ፦** ሽሬ፣ አክሱም፣ አድዋ፣ ተምቤን፣ ምዕ አዲግራት፣ ምዕ ሁለት አውላሎ፣ ምዕ እንደርታ።<br>**ከጎንደር፦** ወገራ፣ ሰሜን፣ ሰምሥ ሊቦ፣ ሰ ጎንደር፣ ሰ ጭልጋ፣ ሰ ጋይንት።<br>**ከወሎ፦** ሰ ላስታ |
| አባይ | **ከጎንደር፦** ደምሥ ጭልጋ፣ በከፊል ደ ጎንደር፣ ደ ጋይንት፣ ደብረ ታቦር።<br>**ከጎጃም፦** ሁሉንም አውራጃዎች።<br>**ከወሎ፦¨፦** ቦረና፣ ወረ ሂመኑ፣ ዋልታ ደላንታ፣ አብዛኛው ወረሂሉ፣ ደ ላስታ፣ ምዕ ወልዲያ፣ አብዛኛው ደሴ ዙሪያ።<br>**ከሸዋ፦** መርሐቤቴ፣ ሰላሌ፣ ሰደም መሀል ሜዳ፣ ሰምዕ ተጉለትና ቡልጋ፣ ሰ መናገሻ፣ አብዛኛው ጅባትና ሜጫ።<br>**ከወለጋ፦** ሁሎ ጉድሩ፣ አብዛኛው ነቀምት፣ አብዛኛው አርጆ፣ ሰምዕምሥ ወለጋ፣ ምሥ አሶሳ፣ ሰምሥ ከለም።<br>**ከኢሉባቡር፦** ሰደ ቡኖ በደሌ።<br>**ከከፋ፦** ሰምዕ ሊሙ። |
| ባሮ አኮቦ | **ከወለጋ፦** ምዕ አሶሳ፣ ምዕደምሥ ከለም፣ ደ ግምቢ፣ ምዕ አርጆ።<br>**ከኢሉባቡር፦** ጋምቤላ፣ አብዛኛው ሞጫ፣ ሶርና ጎባ፣ ጎሬ፣ ም ቡኖ በደሌ።<br>**ከከፋ፦** ጊሚራ፣ ሰምዕ ማጂና ጎልዲያ። |
| አፋር | **ከትግራይ፦** ሰደምሥ አዲግራት፣ አብዛኛው ሁለት አውላሎ፣ አብዛኛው እንደርታ፣ አብዛኛው ራያና አዘቦ።<br>**ከወሎ፦** መሥ ዋግ፣ ምሥ ላስታ፣ አብዛኛው ራያና ቆቦ፣ አብዛኛው ሰ አውሳ፣ ሰምዕ የጁ። |
| አዋሽ | **ከወሎ፦** አብዛኛው የጁ፣ አብዛኛው ደ አውሳ፣ አብዛኛው አምባሰል፣ ቃሉ፣ ምሥ ደሴ ዙሪያ፣ ምሥ ወረሂሉ።<br>**ከሐረር፦** ጨርጨር አዳል ገብረ ጉራቻ፣ ኢሳና ጉርጉራ፣ ሰ ሒብሮ፣ ሰ ወበራ፣ ሰ ሐረር ዙሪያ፣ ሰ ጅጅጋ።<br>**ከሸዋ፦** ምሥ መንዝና ጊሸን፣ ይፋትና ጥሙጋ፣ ሰደምሥ ተጉለትና ቡልጋ፣ ደምዕምሥ መናገሻ፣ የረርና ከረዩ፣ ደምሥ ጅባትና ሜጫ፣ ሰምሥ ጨቦና ጉራጌ፣ ሰ ሐይቆችና ቡታጅራ።<br>**ከአሩሲ፦** ሰምሥ ጭላሎ፣ ሰምዕምሥ አርባጉጉ። |
| ኦሞ ጊቤ | **ከሸዋ፦** ምዕ ጅባትና ሜጫ፣ አብዛኛው ደምዕምሥ ጨቦና ጉራጌ።<br>**ከወለጋ፦** ደቡብ ምሥ ነቀምት።<br>**ከከፋ፦** ሰምሥ ሊሙ፣ ከፋ፣ አብዛኛው ቦንጋ፣ ኩሎ ኮንታ፣ ሰደምሥ ማጂና ጎልዲያ።<br>**ከኢሉባቡር፦** ምሥ ሞቻ፣ ደምሥ ጎሬ።<br>**ከጎምጎፋ፦** ጎፋ፣ ሰ ጋሞ፣ አብዛኛው ገለብና ሐመር ባኮ። |
| ስምጥ ሸለቆ | **ከሸዋ፦** ምሥ ከምባታና ሐድያ፣ አብዛኛው ሐይቆችና ቡታ ጅራ።<br>**ከአሩሲ፦** ሰምዕ ጭላሎ።<br>**ከሲዳሞ፦** ሰደምሥ ወላይታ፣ ደሰምዕ ሲዳማ፣ ደሰምዕ ጌድዮ፣ ሰደምዕ አሬሮ።<br>**ከገሙጎፋ፦** አብዛኛው ሰደምዕምሥ ጋሞ፣ ምሥ ጎፋ፣ ሰደምሥ ገለብና ሐመር ባኮ፣ ጎርዱላ። |
| ዋቢ ሸበሌ | **ከሐረር፦** አብዛኛውን ህብሮ፣ አብዛኛውን ወበራ፣ አብዛኛውን ሐረር ዙሪያ፣ ደምሥ ጨርጨር አዳል፣ ደምዕ ጅጅጋ፣ ጉርሱም፣ ጋራ ሙለታ፣ ሰደምዕ ደገሀቡር፣ ጎዴ፣ አብዛኛውን ቀላፎ፣ አብዛኛውን ከብሪ ደሃር፣ ደምዕ ወልወልና ዋርደር።<br>**ከባሌ፦** አብዛኛውን ሰደምሥ ዋቤ ፣ ግማሽ ሰደምሥ ኢል ከሬ፣ ሰ ዶዶላ፣ ሰምዕ መንደዮ።<br>**ከአሩሲ፦** ጢቾ፣ ደምሥ አርባ ጉጉ፣ ደምሥ ጭላሎ፣ |
| ገናሌ ዳዋ | **ከሲዳሞ፦** ምሥ ሲዳማ፣ ምሥ ጌዴዎ፣ አብዛኛው አሬሮ፣ ጀምጀም፣ ቦረና።<br>**ከባሌ፦** ደምዕምሥ ገናሌ፣ ደሎ፣ አብዛኛው መንድዮ፣ ሰደምዕ ዋቤ፣ ሰደምዕ ኢልከሬ። |
| ኦጋዴን | **ከሐረር፦** ደምሥ ጅጅጋ፣ ደምሥ ደገ ሀቡር፣ አብዛኛው ወልወልና ዋርደር፣ ሰምሥ ቀብሪ ደሀር |
| | |

ምዕ = ም ዕራብ ምሥ = ምሥራቅ ሰ = ሰሜን ደ = ደቡብ መ = መካከለኛው

መ. አዲስ አበባ የከተማ አወቃቀር




*ምሥል 4.0. የቀድሞ አዲስ አበባ ከፍተኞች*

ከላይ በምሥል 4.0 የቀረበው ምሥል በአሁኑ ወቅት ያለውን የአዲስ አበባ አዳዲስ አካባቢዎች ያላካተተ ነው። በደርግ ጊዜ የነበረውን የቀድሞ 25 ቱን ከፍተኞችን በቀጣይነት የተካተቱትን ከፍተኛ 26፣ 27 እና 28ን ብቻ ያካተተ ነው። ሁኔታው ጥናት ተደርጎበት አዲስ የተመሠረቱ አካባቢዎች መካተት ይኖርባቸዋል።

አዲስ አበባን በቀድሞው ከፍተኛ ወይም በወረዳና አውራጃ ማዋቀሩ በአግባቡ ከተጠቀምንበት ለአሠራር ጠቀሜታ አለው። በአሁኑም የክፍለ ከተማ አውራጃና ወረዳ መሠረትም ቢሆን ዋናው ቁም ነገሩ አዲስ አበባን ጨምሮ ሌሎች ከተሞችን በዘርና ቋንቋ ሊዋቀሩ ከቶም የሚያስኬድ እንዳልሆነ ለማሳየት ነው። በ"ኢትዮጵያችን" ዕትም ቅጽ 3 ቁጥር 2 http://www.ethiopiachen.org/images/pdf/Eth_Vol3/070311_1H1H-Ethiopiachin-Vol-3-No-2.pdf በዝርዝር እንደገለጽነው የአንድ ሀገር ግዛታዊ አከላለል ከመንግሥት አስተዳደራዊ መዋቅሮችና አመሠራረት አኳያ የከተሞች ልማትና ዕድገት የተፈጠረውንና የሚፈጥረውን የዜጎች ማንነት ስብጥር አስታኮ በመመልከት ከዘርና ቋንቋ በፀዳ መልኩ መካተታቸው ጠቀሜታው ለሀገር ነው።

## ማጠቃለያ፦

ከላይ ያቀረብናቸው ሦስት አማራጮች ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሲቪክ ማህበራት፣ ምሁራን ወዘተ. ሊያቀርቧቸው ከሚችሉት ጋር ተዛምዶና ለውይይት ቀርቦ ኢትዮጵያ ሀገራችንን እንደ ሀገር ማስቀጠልና የሁሉም ነገድ/ጎሳዎች/ብሔረሰቦች ክልል ኢትዮጵያ እንድትሆን እስከተስማማን ድረስ ዘርንና ቋንቋን መሠረት ያደረግ አከላለል ማብቃት ይኖርበታል ባይ ነን።

ለ28 ዓመት በኢሕአዴግ ብቸኛ አገዛዝ በሀገራችን ላይ የተዘረጋው ዘርንና/ቋንቋን መሠረት ያደረገ አከላለል ሀገሪቱ በዴሞክራሲያዊ ጎዳና እስከተጓዘች ድረስ እንዳለ እንዲቀጥል የሚፈልጉ፣ የሚጥሩ የፖለቲካና የዘር ድርጅቶች እንዳሉ እንገነዘባለን። ሆኖም ግና ይህ የኦሮሞ መንግሥት ነው፣ ይህ የትግሬ መንግሥት ነው፣ ይህ የአማራ መንግሥት ነው . . . እየተባለ የሚደረገው አከላለል ወደድንም ጠላንም የራሱ ያልሆነውን ሌላው ጎሳ/ነገድ/ብሔረሰብ ማግለሉ አይቀሬ ነው። በተጨማሪም በውስጡ ያሉ ንዑሳን ጎሳዎች/ዘሮች/ብሔረሰቦችን ለመዋጥ የሚደረግ ጥረት ሌላ ፖለቲካዊ ጥያቄ እንደሚያስነሳ መገንዘብ አያቅትም። በሌላ መልኩ ደግሞ አዲስ አበባን ጨምሮ በሌሎች በተለይ የከተማ ነዋሪው ኅብረተሰብ ዘርና ጎሳው በኢትዮጵያዊነት ላይ ብቻ የተመሠረተና ክልል የሌለቸው በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሀገሪቷ ዜጎች ላይ ሊፈጥር የሚችለው ችግር ሊታየን ይገባል። በመሆኑም ሀገራችን ኢትዮጵያ፣ ክልላችን ኢትዮጵያ፣ ልማታችን ለኢትዮጵያ፣ ዕድገታችን ለኢትዮጵያ እስካልን አኩሪ ባህሎቻችንን፣ ቋንቋዎቻችንን እያሳደግንና እየተንከባከብን ዓለም እደረሰበት ብቻ ሳይሆን ከፍ ብለንም ለመውጣት ከፈለግን ዘርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገ ሀገራዊ አከፋፈል ማብቃት ይኖርበታል።

ለብዙ ሺህ ዓመታት ጠንክሮ የነበረው ኢትዮጵያዊነት በነበረበት አስተዳደራዊ ችግርና ኢ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ሰበብ ሁኖ አንድ ዘር/ነገድ/ብሔር ገዢና ፈላጭ ቆራጭ ተደርጎ ያመጣው መስመሩን የሳት "የብሔር ብሔረሰቦች መብት እስከመገንጠል" መፈክር ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጵያ ለተዘፈቀችበት አጣብቂኝ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማድረጉ ሊታበል አይገባም። በተለይ ከታላቁ የዐድዋ ድል በኋላ ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት እየጎለበተና እያበበ ቢመጣም በተከታታይ የነበሩት የዓፄ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ብዙ ማስተካከል ሲችሉ ባለማድረጋቸው፣ የደርግ አገዛዝ ፍትሃዊነት ማጣትና ጦረኝነት በየአካባቢውና በየዘሩ ያቆጠቆጡ እንቅስቃሴዎች ይበልጥ እንዲጠናከሩ አደረጋቸው። ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ትግራይን "ነፃ" ሊያወጣ የተንቀሳቀሰው "ህወሓት" ከፋፋይ መንገዱ ሰምሮለት ኢትዮጵያን በዘርና በቋንቋ ለመሸንሸን ጊዜም አልፈጀበት። ያም ቢሆን በዚህ 28 ዓመት አገዛዙ በዘር የከፋፈለው ኅብረተሰብ ዛሬም ኢትዮጵያዊነቱን አፍቃሪ፣ ለሃይማኖቱ ተገዥ፣ ባህሉን አክባሪ ነውና የኢሕአዴግን ዘረኛ አከላለል ለማስወገድ ምንም የሚቸግረን አይሆንም።

ከላይ የተቀመጡትን በተለይ አውራጃንና ተፋሰስ ወንዞችን መሠረት ያደረገ አከላለል በአንድ ጀምበር ተግባራዊ ይሆናል ተብሎ አይጠበቅም። በቅድሚያ በሀገራችን ያለምንም ገደብ የግለሰብና የዜግነት መብት ተግባራዊ እስከሆነ ድረስ ማንም በዘሩ ተከልሎ አይኖርምና ተፈላጊውን ሰላም በማምጣት የልማቱንም፣ የእድገቱንም እንቅስቃሴ በመረባረብ ስኬታማ ለማድረግ ሕዝባችን ለጉልበቱ እንደማይሳሳ በድፍረት መናገር ይችላል። መብትና ዳቦ በመጠየቃቸው ልጆቹን ለወያኔ ጥይት የገበረ ሕዝባችን ለሀገር ፍቅርና ለኢትዮጵያዊነት ግንባታ ገንዘብና ጉልበቱን ሳይጠየቅ እደሚቸር በመገንዘብ የጉዞ አቅጣጫችን ይሠምር፣ ቀና ይሆን ዘንድ ከላይ የተጠቀሱትን አከላለሎች "ልማታዊ አከላለል" በማለት እየተለመዱ እንዲሄዱ ማድረግ ይቻላል።

**አሁን ያለው የዘር አከላለል ይበልጥ የሚገላበጠው በአለው የኢሕአዴግ አገዛዝና በአንዳንድ የዘር ፖለቲካ ድርጅቶች እንዲሁም በተማረው ምሁራን አካባቢ እንጂ የኦሮሞ አርሶአደሮች፣ የአማራ አዛውንቶች፣ የትግራይ ገጠሬዎች፣ የከተማ ልጆች፣ የኢትዮጵያ ቄሮ፣ ፋኖዎች፣ ታዳጊ ሕፃናት፣ ወጣቶች፣ ሴቶች አሁንም ኢትዮጵያችንን አፍቅረው፣ ዘር ሳይመርጡ ተጋብተው፣ በሁሉም ባህል አብበው፣ ለሃይማኖታቸው ተገዝተው ሌላ ሌላም ለመኖር ኢትዮጵያዊነትን ይመርጣሉ፣ ከፍ ያደርጋሉና ቅንነቱ ካለ ዘርና/ቋንቋን ያላማከለ አስተዳደራዊ አከላለል ተግባራዊ ማድረጉ አይከብድም።**

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!**

***ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ!***

**አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ**

**የዚህ ሠነድ የባለቤትነት መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።**

**ግንቦት** 4 **ቀን** 2011 **ዓ.ም**. (May 12, 2019)

**ማሳሰቢያ ፡**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» «***ኢትዮጵያችን***» ልሳን በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ስልክ፡ **703 300 4302**
ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org , www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachin

ኢትዮጵያችን